የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)
Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)
www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com

# ከድጡ ወደማጡ ! !

ለህዝብ ደንታ የሌለውና የወዳጅ ምክር የማይቀበል መንግስት የመጨረሻ እጣ ፈንታው መወገድ ነው።

ላለፉት ሃያስድስት ዓመታት በጉልበት ስልጣኑን ጨብጦ ያሻውን ሲያደርግ የኖረው የአምባገነን የዘረኞች ቡድን ከአሁን በኋላ እያጭበረበረና እየዋሸ፣እየገደለና እየዘረፈ የሚኖርበት ዘመኑ እየተመናመነ መምጣቱን የሚያመለክቱ ሁኔታዎች ተከስተዋል።ስልጣን ለመያዝና ከያዘም በኋላ እንዳይወርድ ሲንከባከቡትና ሲረዱት የነበሩት አጋሮቹ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ጀርባቸውን እየሰጡት መጥተዋል።ይህ የሆነበት ምክንያት ስርዓቱ ን እንደፈረስ ሊጠቀሙበት የሚችሉበት አስተማማኝ ዕድል በህዝቡ ትግል እየተናደ በመምጣቱና ስርዓቱም ከድጡ ወደማጡ እየተዘፈቀ መመጣቱን በማጤን ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ እንዳይሆንባቸው በማሰብ ነው።

ይህን ተመልክቶ ሰሞኑን የአውሮፓ ህብረት የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ የሆነው አካል የኢትዮጵያ መንግስት በህዝቡ ላይ የፈጸመውንና እየፈጸመ ያለውን በተለይም በ2016 ታህሳስ ወር ላይ በደብረዘይት (ቢሸፍቱ) የእሬቻ በዓል ላይ የፈጸመውን ግፍና ጭፍጨፋ በሚመለከተው አድራጎቱን በማውገዝ በአስቸኳይ የተባበሩት መንግስታት አጣሪ ቡድን እንዲመሰረት የሚጠይቅ መግለጫ ያወጣ ሲሆን ይህንኑ ጉዳይ በሚመጣው ወር ውስጥ በጀኔቫ በሚካሄደው የሰብአዊ መብት ድርጅት ስብሰባ ላይ ቀዳሚ አጀንዳ ነጥብ አድርጎ ለማቅረብ ወስኗል።

በተመሳሳይም በአሜሪካ በኩል የዋሽንግተን ዲሲ የሴኔት ምክር ቤት አባል የሆኑት ሴናተር ማርኮ ሩቢዮ ከሜሪላንድ ሴናተር ከሆኑት ከበን ካርዲን ጋር ግምባር ቀደም በመሆን ሌሎች በርከት ያሉ የሴኔት አባላትን አስተባብረው ጉዳዩ ትኩረት እንዲያገኝና በምክር ቤት ደረጃ አቋም እንዲወሰድበት የሚጠይቅ እረቂቅ ለውሳኔ አቅርበዋል።የሴኔት አባላቱ ከዚህም በተጨማሪ በእስር ላይ የሚገኙት የተቃዋሚ ድርጅት አባላት፣ጋዜጠኞች፣የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች፣ ጠበቆች . . . ወዘተ ካለምንም ቅድመሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ ጠይቀዋል።

በአውሮፓውያኑና በአሜሪካኖቹ የቀረበው ጥያቄና ዝርዝር መግለጫ የህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት በየጊዜው የሚፈጽመውን በደልና ግፍ ከውግዘት ባለፈ መልኩ በወንጀለኛነት የሚጠይቅ ነው።በአሜሪካኖቹ በኩል ምንም እንኳን የኢትዮጵያ መንግስት ለጸረ ሽብር ትግላችን አጋር ቢሆንንም በራሱ ህዝብ ላይ የሚፈጽመውን ሽብር በዝምታ ልናልፈው አይገባንም ብለዋል።

ይህ በእንዲህ እያለ ካፈርኩ አይመልሰኝ ያለው የወያኔ መራሹ ስርዓት አሁንም በየቀኑ የሚቀርብለትን ምክርና አቤቱታ እረግጦ በመላ ያገሪቱ መሬት በዜጎች ላይ የሚያደርገው ግድያ፣አፈና፣ማሳደድ፣ማሰርና ማሰቃየት እንደቀጠለ ነው። ለሰብአዊ መብት መከበር፣ለህግ የበላይነት ሲሉ ድምጻቸውን ያሰሙ ሁሉ ከበቀል ዱላ አልተረፉም፤ያ የበቀል ዱላ ደግሞ ሞትና መሰወርን ያጠቃልላል።

በሸዎች የሚቆጠሩ እየታፈሱ እስር ቤቶች ተጣበዋል፤ካለፍርድ ለዓመታት የታሰሩትና መድረሻቸው ያልታወቀውን ቤት ይቁጠራቸው እንጂ በስም መዘርዘር አይቻልም።በፍርደገምድል ዳኞችና የስርዓቱ ቡችሎች የዜግነትና ሰብአዊ መብታቸው እየተጣሰ ለዓመታት እስራት ተበይኖባቸው የሚሰቃዩት የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና አባላት፣ጋዜጠኞች፣ ጠበቆች፣የማህበረሰብ ተወካዮች ቁጥር ከቀን ወደቀን እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም።ይህም ሆኖ ግን ህዝቡ ለመብቱ የሚያደርገውን ትግል እንዲቀጥልበት አደረገው እንጂ በፍርሃት እንዲንበረከክና እንዲያፈገፍግ አላደረገውም።ለዚህ በየቦታው የሚካሄደው ህዝባዊ ትግል ማስረጃ ነው።በፍርሃት ተጠምዶ ጊዜያዊ አስቸኳይ አዋጅ አውጆ የመንቀሳቀስ መብት ለመንፈግ የተገደደው ህዝባዊ ድጋፍ አለኝ ብሎ የሚኩራራው መንግስት ነኝ ባዩ አጥፊ ቡድን እንጂ ህዝቡ አይደለም።በወንጀል ላይ ወንጀል መፈጸምን ባህልና ችሎታ አድርጎ የወሰደው የገዥው ማፊያ ቡድን አገር ውስጥ ካሉት ተጠቃሚዎችና ከራሱ ደጋፊዎች ብቻ ሳይሆን እውጭ ካሉትም አጋሮቹ ጋር የየተነጠለ

መምጣቱን በአውሮፓውያኑና በአሜሪካኖቹ በኩል የታየው መንሸራተት ማስረጃ ነው። በዚህ ቀውስ ውስጥ የተዘፈቀው ቡድን በራሱም ውስጥ ሁከትና ጭቅጭቅ ብሎም መከፋፈል እንዳመጣ የሚያሳዩ ምልክቶች እየወጡ ነው።እርስ በርስ ለመበላላት ወይም  አገርን  ትርምስምስ ውስጥ ከቶ ለመጥፋት በየፊናቸው መውጫ ቀዳዳ በማሰስ ላይ መሆናቸው በገሃድ እየተነገረ ነው።ጥያቄው ግን መቼና የት በሰላም ሊኖሩ ይችላሉ የሚለው ነው።

«ብረት እንደጋለ! ጠላት እንደተከፋፈለ ነውና  በውስጡ የተፈጠረውን ቀውስ በማቀጣጠል  እንዲሁም  ለስርዓቱ አጋር ሆነው ሲደግፉ የነበሩት አሁን የህዝቡ ትግል እያሳሰባቸው በመምጣቱ ሲገለገሉበት የነበረው ፈረስ እየደከመና እያረጀ መምጣቱን በማየት ያደረጉትን መንሸራተት  በመጠቀም የሚያሰሙትን የተቃውሞ ድምጽ በማስተጋባት የህዝቡን ያላሰለሰ ትግል ለድል ለማብቃት በውጭ አገር የሚኖረው አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ተባብሮ ለድምጽ አልባ ወገኖቹ ድምጽ ሆኖ፣ለመበታተን አደጋ የተጋለጠች አገሩን ለማዳን በሚደረገው ትግል እንዲሳተፍ ሸንጎ በተለያዩ ጊዜያቶች ያደረገውን ጥሪ አሁንም በድጋሚ ያስተላልፋል።

የግፈኞችና የአምባገነኖች ስርዓት እንጂ የህዝብ ትግል አይሞትም

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!

የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)